# የመጽሐፍ ግምገማ

## ከመቆየት መልካሙ

ደራሲ፡ ፕሮፌሰር፡ ጌታቸው ኃይሌ
ርእሱ፡ **አንጻፍታ ላውጋችሁ**
የገጹ ብዛት፡ 327
ዋጋው፡ 19.95 ዶላር
የታተመበት ዘመን፡ 2001 ዓ.ም.

ደራሲው የሕይወት ታሪካቸውን በዚህ በዳጎሰ መጽሐፍ እጅግ ውብ በሆነ የአጻጻፍ ስልት ለአንባብያን አቅርበዋል፡፡ የግል ሕይወት ታሪካቸውን የመዘገቡበት ይህ ዜና መዋዕል፥ በ59 ልዩልዩ ፎቶግራፎች፥ በበርካታ ሰነዶችና በታሪካዊ ማስረጃዎች የደገፈ ነው፡፡ የደራሲ ጌታቸው ኃይሌን አውቶባዮግራፊ እስካሁን ካነበብኳቸው ሌሎች በግል ከተጻፉ የሕይወት ታሪክ መጻሕፍት ልዩ የሚያደርጉት፥ በርካታና ዓይነተኛ የሆኑ ነጥቦች ሊኖሩ ቢችሉም፥ በእኔ ትዝብት፥ በግልጽነቱ፥ በቋንቋ ጥራቱ፥ በሥነ ጽሑፍ ውበቱ፥ በሆሄህያት አመራረጥ ትክክለኝነቱና አያሌ ዝርዝር መዘክሮችን መመዝገቡ ነው፡፡ ከውጭ ዜጎች ደራሲያን ካነበብኳቸው መጻሕፍት መካከል፥ በግልጽነቱ ብቻ፥ የእስራኤል ጠቅላይ ምንስትር የነበሩት ሚቿ ጎልዳ ሜየር *My Life* እና የግብጹ ፕሬዝደንት የነበሩቱ አንዋር ኤል ሳዳት
*In Search Of Identity*
በተሰኙ የግል ታሪኮቻቸውን ከመዘገቡት መጻሕፍቶቻቸው ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው ተገንዝቢያለሁ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ በአማርኛ ከተጻፉት የግል ታሪኮች መካከል፥ ማስታወስ የምችለው፥ በአለፈው ኅዳር ወር ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ብርጋዴር ጀኔራል ታምራት ተሰማ ያሳለፍኩት ዘመን ከተሰኘው መጽሐፋቸው ጋር ከሞላ ጎደል ይቀራረባል፡፡

በፕሮፌሰር ጌታቸው መጽሐፍ ውስጥ ለአንባብያን የቀረበላቸው አዲስ ትውውቅ፥ በድርሰቱ መጨረሻዎቹ ገጾች ላይ አቶ አምሃ አስፋው የጨመረው መጠቍም ወይም ፈረንጆቹ ኢንዴክስ የሚሉት እንደሆነ ለመማር በቅቻለ፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸውና አቶ አምሃ በዚህ መጠቍም ባሉት ርእስ ስር የተመዘገቡት ሁሉ፥ በአማርኛ የፊደል ተራ ቅድም ተከተል በመሆኑ፥ አንባብያን ወደ ገጾቹ እየተመለሱ ለማመሳከር እንዲመቻቸው ሆኖ የተሰናዳ ነው፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ይህ መጠቍም በእንግሊዝኛ የፊደል ተራም ተመዝግቧል፡፡ በዚህ አኳያ፥ ደራሲውና ረዳቱ፥የተዋጣለት ክንዋኔ ፈጽመዋል ማለት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ደራሲ ጌታቸው ኃይሌ፥ በዚህ የግል ሕይወታቸውን በመዘገቡበት መጽሐፍ ውስጥ፥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፉ የሚችሉ ጠቃሚነታቸው፥ለሀገራችን ኢትዮጵያ ታሪክና ቅርስ በማስረጃ ያቀረቡት፥ ከአንድ እስከ ሠላሳ ሦስት ተራ ቁጥር በዛት ያላቸው በኢትዮጵያ የረዥም ዘመን ታሪክ የነበሩ መዛግብት ናቸው፡፡ እነዚህ መዛግብት፥በ7 ቅጾች (Volumes) የታተሙ ናቸው፡፡ ደራሲ ጌታቸው ኃይሌ ይህንን በማድረጋቸው "ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከአንድ መቶ ዓመት ወዲህ የተፈጠረች ነች" የሚሉ ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎችን ከንቱ ሐሳብ ዕርቃነ ሥጋ ማስቀረታቸው ነው፡፡ ይህንን ያደረጉት፥ በሚያገለግሉበት የቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርስቲ በማይክሮፊልም የተከማቹትን የጥንት መጻሕፍትን ለሠላሳ ዓመታት ያህል በመመርመርና ካታሎግ በማድረግ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በቋሚ ማስረጃ የተደገፈ የአያሌ ዘመን ታሪክ ሀገር ባለቤት መሆኗን ባጋጠማቸው ቍጥር በተደጋጋሚ አስረድተዋል፡፡ ይህ ክንዋኔ የቱን ያህል አድካሚ፥ትግዕስት አስጨራሽና ካባድ ተግባር መሆኑን የሚረዳው፥ በሙያው የተሰማራ ብቻ እንደሚሆኑ ይሰማኛል፡፡ ደራሲው ይህንን ለሀገርና ለትውልድ የሚጠቅም ተግባር በመፈጸማቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል ብየ አምናለሁ፡፡

በአንጻፍታ ላውጋችሁ የተዘረዘረው ታሪክ የደራሲው የግል ታሪክ መሆኑን ብረዳም፥ መጽሐፉን በሚገባ ለአነበበውና ከአድማስ ባሻገርም ለማየት የሚችል አንባቢ ሊረዳው

የሚችለው፥ የሀገሩንም ታሪክ ጭምር ይሆናል ብየ ብናገር እንደማገነን ሊቆጠርብኝ እንደማይችል እገምታለሁ። በመሠረቱ፥ የአንድ ሀገር ታሪክ ማለት፥ የዜጎቿ የየግል ታሪኮች ድምር ውጤት መሆኑን ግን ደግሞ እየተረዳሁም ጭምር ነው።የአንጻፍታ ላውጋችሁ ደራሲ በዚህ የግል ታሪክ መጽሐፋቸው፥ ከመጀመሪያው ገጽ እስከ መጨረሻው ድረስ የተገለጸውን ታሪክ ለመዘርዘር አልቃጣም፥ ይህንን ማንኛውም አንባቢ አንብቦ እንደ እኔ ብዙ ታላላቅ ጠቃሚ ትምህርቶች ይገበይበታል ብየ ስለማምን ወደዚያ አቅጣጫ ከማምራት ተቆጥቢያለሁ። መጸሐፉን በማንበቤ፥ የሰው ልጅ፥ የደረሰበትን አሰቃቂ መከራና ከባድ ፈተና፥ በትዕግስት፥ በሞራል ጥንካሬ፥ በእምነት ጽናትና፥ በማይበገር ብርቱ ሰብእና መቋቋም ብቻ ሳይሆን፥ተቋቁሞም አስደናቂ ተግባር ማከናወን እንደሚችል ለመማር በቅቻለሁ። በታሪኩ እንደተዘረዘረው፥ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በታሪካቸው የደረሰባቸውን ካባድ ፈተና ሊቋቋሙ የቻሉት፥በደስታውምይሁን በችግሩ ጊዜ ከጎናቸው አብረው በቆሙት ባለቤታቸው፥ በወይዘሮ እሜቱ (ምሥራቅ) አማረ ያልተቆጠበ ፍቅር፥ ምክርና ትብብር መሆኑን ሲረዳ፥አንባቢው ሁሉ፥ለዚች መንፈሰ ጠንካራ ኢትዮጵያዊት የተለየ አክብሮትና ምስጋናውን እንደሚያጎርፍላቸው ምንም ጥርጥር አይኖርም።

አንጻፍታ ላውጋችሁ፥ የአጻጻፉ ስልትና ይዘት፥ የአተራረኩና የቋንቋው ዘየ በተራቀቀ የምሁርና የአስተማሪ አቀራረብ የተዘጋጀ ስለሆነ፥ ምናልባት ለተራ አንባቢ ትንሽ ያስቸግር ይሆናል የሚል አነስተኛ ስጋት አለኝ።እንዲያው ዛሬ በጎሳ ሥርዓት የምትተዳደረው ሀገራችን በክልል በመሸንሸኗ ምክንያት ያንዱን ክልል ቦታ ስም በሌላ ክልል ውስጥ ባለ ስም መጥራት፥ ምናልባት ዘረኞችን ያቃጥላቸው ይሁን ከሚል "ስጋት" ከመነጨ ብቻ የለማሊሞን ስም ለአላማጣ ማዘዋወር እንደ ዐቢይ ሕፀፅ ባይቆጠርም ፥ ስለ ሁለቱ ተራሮች በልጅነቴ የሰማኋቸውን ግጥሞች ለማስታወስ ብየ አጋጣሚውን ለመጠቀም በመቻሌ ደራሲውን አመስግናለሁ።

የዛሬውን አያድርገውና ድሮ፥ የአስመራ ነጋዴዎች ወደ ጎንደር ሲመጡ የሚከተለውን ግጥም በትግርኛ ቋንቋ ይገጥሙ እንደነበር አስታውሳለሁ።

"መንገዲ ጎንደር ለማሊሞ፥
ከመይ አለኺ እሞ።"

ሲተረጎም፥

"የጎንደር መንገድ ለማሊሞ፥
እረ እንደምን አለሽ።"

ማለት ነው።

ስለ አላማጣ ገደል ደግሞ፥

" አላማጣ ሄጄ መልሼ አላማጣ፥
ከበሽታይ ላይ በሽታ ላመጣ።"

ሲል አንድ ወሎየ ጎረምሳ አዜመ ይባላል። ደራሲው የዋልድባን ገዳም ለመጎበብኘት ያለፉበት ገደል ስም ለማሊሞ እንጅ አላማጣ እንዳልሆነ አንባቢያን በቅድሚያ እንዲረዱት ለመጠቆም እንጅ፥ ጉዳዩ ይህንን ያህል ጫና ያለው ሆኖ አይደለም።

የፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ አንጻፍታ ላውጋችሁ መጽሐፍ ፥ሁሉም ሰው ግዝቶ ቢያነብበው ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶች ያገኝበታል ብየ አምናለሁ። ደራሲውንም ይህን የአማርኛ አጻጻፍ መምህርነታቸውን ያሳዩበትን ሥራቸው ስላሳተሙ እንኳን ደስ ያለዎ እላለሁ።